
# <u>እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 21-28/2019 የነበረው</u>
# <u>የአየር ሁኔታ ግምገማ</u>

ባለፉት የፌብርዋሪ ስምንት ቀናት ፀሃያማ እና ደረቃማ የአየር ሁኔታ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ አመዝኖባቸዉ ነበር የተስተዋለዉ፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም የቀኑ ከፍተኛ ሙቀት በአንዳንድ የሀገሪቱ ቆላማ ስፍራዎች ላይ ይበልጥ ጨምሮ ተስተዉሏል፡፡ ይሁን እንጂ አልፎ አልፎ ከነበረዉ ደመና በሰሜን ምስራቅ፣ በመካከለኛዉ፣ በደቡብ እና ደቡብ ምዕራብ አካባቢዎች ላይ ዝናብ እንደነበረ መገንዘብ ተችሏል፡፡ በዚሁ መሰረት ባለፉት ስምንት ቀናት በምስራቅ እና ምዕራብ ጎጃም፣ በሰሜን እና ደቡብ ወሎ፣ በጋምቤላ ዞኖች፣ በምስራቅ፣ ቄለም እና ምዕራብ ወለጋ ዞኖች፣ በከፋ፣ በሸካ፣ በጉራጌ፣ በስልጤ፣ በሲዳማ እና በጋሞጎፋ ዞኖች በአንዳንድ ቦታዎቻቸዉ ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እንዲሁም አልፎ አልፎ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ በስምንቱ ቀናት ውስጥ ከባድ ዝናብ ከመዘገቡ ጣቢያዎች መካከልለመጥቀስ ያህል በወረኢሉ 46.7 እንዲሁም በጊኒር 48.0 ሚ.ሜ መጠን ያለው ከባድ ዝናብ ተመዝግቧል።


ባለፉት ስምንት ቀናት የዘነበው የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ የቦታ ሽፋን አንጻር ሲገመገም ከ5-59 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከአማራ ሰሜን ሸዋ፣ ሰሜን እና ደቡብ ወሎ፣ ደቡብ ጎንደር፣ ምዕራብና ምስራቅ ጎጃም፤ ከኦሮሚያ ምስራቅ፣ ቄለም እና ምዕራብ ወለጋ፣ ጅማ፣ ኢሉአባቦራ፣ ምዕራብ ሸዋ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ፣ ባሌ፣ ጉጂና ቦረና፤ አብዛኛዎቹ የደቡብ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ዞኖች እና ጋምቤላ ክልል ዞኖች ከ1-5 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2) ።

ባለፉት ስምንት ቀናት የዘነበው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር ሲነጻጸር በምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ፤ በሁሉም የወለጋ ዞኖች፣ በምዕራብ ሸዋ፣ በኢሉአባቦራ፣ በጅማ እና በባሌ፤ በጋምቤላ እና በደቡብ ብሄር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ዞኖች፤ በደቡብ ጎንደር፣ በምዕራብ እና ምስራቅ ጎጃም እንዲሁም በሰሜን ሸዋ ኪስ ቦታዎች ላይ መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ ዝናብ የነበራቸው ሲሆን፤ የተቀሩት የሀገሪቱ ክፍሎች ደግሞ ከመደበኛው በታች የሆነ ዝናብ አግኝተዋል (ካርታ 3) ።


ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከፌብሪዋሪ 21 እስከ 28 /2019 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከፌብሪዋሪ 21 እስከ 28 /2019 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት




## ካርታ 3  እ.ኤ.አ ከፌብሪዋሪ 21 እስከ 28 /2019 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን
## ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



# <u>ኢ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 21-28/2019 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርናው ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ</u>

ባለፉት ስምንት ቀናት ፀሃያማ እና ሞቃታማ የአየር ሁኔታ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ አመዝኖባቸዉ ነበር፡፡ ከዚህም ጋር በተያያዘ የቀኑ ከፍተኛ ሙቀት በአንዳንድ የሀገሪቱ ቆላማ ስፍራዎች ላይ ይበልጥ ጨምሮ ተስተዉሏል፡፡ ይሁን እንጂ አልፎ አልፎ ከነበረው እርጥበት በምስራቅ እና በምዕራብ ጎጃም፣ በሰሜንና ደቡብ ወሎ፣ በጋምቤላ ዞኖች፣ በምስራቅ፣ በቄለም እና በምዕራብ ወለጋ ዞኖች፣ በከፋ፣ በሸካ፣ በጉራጌ፣ በስልጤ፣ በሲዳማ እና በጋሞጎፋ ዞኖች በአንዳንድ ቦታዎቻቸዉ ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት ነበራቸው፡፡ ይህም ሁኔታ ለበልግ አብቃይ አከባቢዎች ለበልግ እርሻ ሥራዎች፣ ለአፈር እርጥበት መጠናከርና ለዘር መዝራት ፣ ለእንሰሳት የመጠጥ ውሃ አቅርቦት፣ ለአረንጓዴ ተክሎች ልምላሜና ለጓሮ አትክልት እንዲሁም ለከብቶች የመኖ አቅርቦት ምቹ ሁታዎችን የፈጠረ ነበር ፡፡


ካርታ 4 ኢ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 21 እስከ 28/2019 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



# እ.ኤ.አ  ከፌብሪዋሪ 21-28/2019 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅሰቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅኖ

እ.ኤ.አ ከ21-28 ፈብርዋሪ 2019 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረውን ተፅዕኖ ስንመለከት መካከለኛው ስምጥ ሸለቆ፣ ኦሞና ዋቢ ሸበሌ፣ ደቡብና ምስራቅ አባይ፣ ባሮ አኮቦ እንዲሁም ኦሞ ጊቤ ከፍተኛ እርጥበት ያገኙ ሲሆን፤ የላይኛው ባሮ አኮቦና ግናሌ ዳዋ በተጨማሪም ጥቂት የላይኛው ዋቢሸበሌ ተፋሰሶች መጠነኛ እርጥበት ያገኙ ሲሆን፤ የተቀሩት ተፋሰሶች ከከፊል ደረቅ እስከ ደረቃማ ሁኔታ ላይ ሰንብተዋል፡፡ ይህም ሁኔታ ለበልግ ተጠቃሚ አካባቢዎች አዎንታዊ ሁኔታ እንደነበራቸው ተስተውሏል (ካርታ 5)፡፡

ካርታ 5. እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 21 እስከ 28/2019 በተፋሰሶች ላይ የነበረው የእርጥበት መጠን



# እ.ኤ.አ ከማርች 1-10/2019 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ በማርች የመጀመሪያው አሥር ቀናት የበልግ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ከዕለት ወደ ዕለት አንፃራዊ መጠናከር እያሳዩ በመሄድ የወቅቱ ዝናብ በበልግ አብቃይ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ እየተስፋፋና እየተጠናከረ ይመጣል።

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በበልግ አብቃይ ሥፍራዎች ላይ እምብዛም ጥንካሬ ሊኖራቸው እንደማይችልና በአብዛኛው የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ደረቃማ የአየር ሁኔታ እንደሚያመዝን የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

በአጠቃላይ በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ከኦሮሚያ ክልል ጅማ፣ ኢሉአባቦራ፣ ምዕራብና ምሥራቅ ወለጋ፤ የአርሲና የባሌ ዞኖች፣ ሰሜን ሸዋ፣ የምዕራብና ምሥራቅ ሐረርጌ፤ አዲስ አበባ፤ ከአማራ ክልል ሰሜንና ደቡብ ወሎ፣ ሰሜን ሸዋ፣ ምሥራቅ እና ምዕራብ ጎጃም እንዲሁም ደቡብ ጎንደር፤ ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ደግሞ የወላይታ፣ የዳውሮ፣ የጋሞጎፋ፣ የከፋና የቤንች ማጂ፣ የጉራጌ፣ የሀዲያና የሲዳማ ዞኖች በአንዳንድ ቦታዎቻቸው ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛው መጠን ያለው ዝናብ ይኖራቸዋል። የተቀሩት የሀገሪቱ አካባቢዎች በአመዛኙ ደረቅ ሆነው ይሰነብታሉ።

# እ. ኤ. አ ከማርች 1-10/2019 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመደበኛ ሁኔታ በማርች የመጀመሪያው አሥር ቀናት የበልግ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ከዕለት ወደ ዕለት አንፃራዊ መጠናከር እያሳዩ የሚሄድበትና የወቅቱ ዝናብ በበልግ አብቃይ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ እየተስፋፋና እየተጠናከረ የሚመጣበት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ለበልግ እርሻ ሥራ የማሳና የዘር ዝግጅት የሚጠናከርበት እንዲሁም በአንዳንድ ቦታዎች የዘር መዝራትሥራዎች የሚጀምሩበት ወቅት ነው፡፡

ከላይ በተሰጠዉ ትንበያ መሰረት በሚቀጥሉት አስር ቀናት በጅማ፣ በኢሉአባቦራ፣ በምዕራብና በምሥራቅ ወለጋ፣ በአርሲ፣ በባሌ፣ በሰሜን ሸዋ፣ በምዕራብና ምሥራቅ ሐረርጌ፣ በአዲስ አበባ፣ በሰሜንና ደቡብ ወሎ፣ በሰሜን ሸዋ፣ በምሥራቅ እና ምዕራብ ጎጃም፣ በደቡብ ጎንደር፣ በወላይታ፣ በዳውሮ፣ በጋሞጎፋ፣ በከፋ፣ በቤንች ማጂ፣ በጉራጌ፣ በሀዲያና በሲዳማ ዞኖች በአንዳንድ ቦታዎቻቸው ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው እርጥበት እንደሚኖራቸዉ ይጠበቃል፡፡ ይህም ሁኔታ በልግ አብቃይ ለሆኑት አከባቢዎች ለበልግ እርሻ ሥራ እንቅስቃሴዎች አውንታዊ ጎን  እንደሚኖረው ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትና አርሶአደሩ ለበልግ እርሻ የማሳ ዝግጅትና የዘር መዝራት ሥራዎች አጠናክሮ እንዲቀጥሉ ይመከራል፡፡ በተጨማሪም ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለመጠጥ ውኃና ለግጦሽ ሳር አቅርቦት አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል፡፡  ሆኖም የሚጠበቀው ዕርጥበት ሙሉ ለሙሉ ፍላጎትን የሚያሟላ ላይሆን ስለሚችል የተገኘውን እርጥበት በአግባቡ መያዝና እንዳይባክን የመጠበቂያ ስራዎች በስፋት መከናወን ይኖርባቸዋል፡፡

## <u>እ. ኤ. አ ከማርች 1-10/2019 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በውሃው ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ</u>

በሚቀጥሉት አስርት ቀናት በተሰጠው ትንበያ መሰረት በውሃው ዘርፍ ላይ የሚኖረው ተፅዕኖ ስንመለከት ከዝናብ ሰጭ ክስተቶችጋር ተያይዞ በአብዛኛው የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ በመጠኑም ቢሆን የእርጥበት መጠን እየጨመረ እንደሚሄድ ትንበያው ያመለክታል፡፡ በመሆኑም አብዛኛው አባይ፣ ባሮ አኮቦ ኦሞ ጊቤ መካከለኛውና የላይኛው ስምጥ ሸለቆ፣ በጥቂት የላይኛውና መካከለኛው ዋቢሸበሌ፣ ደቡብ ምዕራብ አፋር ደናክል፣ የላይኛው ተከዜ ተፋሰሶች መጠነኛ እርጥበት የሚኖራቸው ሲሆን፤ የተቀሩት የሀገሪቱ ተፋሰሶች ደረቀ ሆነው ይቆያሉ፡፡ በመሆኑ እርጥበት ያለባቸው አካባቢዎች ላይ በተቻለ መጠን የሚገኘውን የዝናብ ውሃ በአግባቡ በመያዝ ጥቅም ላይ ማዋል ተገቢ ነው፡፡